የኢትዮጵያ ግብርና
ባለስልጣን
Ethiopian Agricul-
tural Authority

# ዜና ሠፀሐት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 71 ጥቅምት 2018 ዓ.ም

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት፡፡
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ 31303

ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520

የውስጥ መስመር፡- 227/234

ዌብሳይት:- http:www.eaa.gov.et

ፌስቡክ:- Ethiopian Agricultural Authority

ቴሌግራም:-eaapr_1234

## ባለስልጣኑ ከ188 አገራት ጋር ትስስር ያደረገውን ዲጂታል የኤሌክትሮኒክ ኢፋይቶ(ePhyto System) ስረዓት ማስጀመሩን ይፋ አደረገ ።





የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ብሔራዊ የዕፅዋት ጤና ጥበቃ (ePhyto System) ስረዓት ላይ ያተኮረ ኮንፈረንስ አካሄደ ።

የኮንፈረንሱ ዋና ዓላማ ውጤት ያለው ውይይት ለመፍጠር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ ንግድን ለማስተዋወቅ እና የግብርና ኤክስፖርት ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እና ቀጣናዊ ትስስርን ለማጠናከር ያለመ ነው።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ባለስልጣኑ ሁሉንም 66 አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ አድርጎ እየሰራ መሆኑን ገልፀው 29ኙን ደግሞ በመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ውስጥ አካትቶ እየሰጠ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ እክለውም ይህ የዲጂታል ኤሌክትሮኒክ ePhyto Sistem ስረዓት መጀመሩ የዓለም ንግድ ድርጅቶች የእፅዋት ምርቶችን በተመለከተ የሚያወጧቸውን መስፈርቶች ለማሟላት ያስችላል ብለዋል፡፡

ታማኒነት ያለው የንግድ ስርዓት እንዲፈጠርም ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ 2 ዞራል!

ከገጽ 1 የዞረ..

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የእፅዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወንዳለ ሃብታሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኢፋይቶ(ePhayto) ሥርዓት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ እና ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ጥራት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ ዲጂታል ስረዓት ነው ብለዋል።

ይህ የዲጂታል ኤሌክትሮኒክ ePhyto ሲስተም 188 የዓለም አገራት ጋር ትስስር መፍጠሩን ገልፀው የሲስተሙ መጀመር በንግዱ የተሳሰሩ ሀገራትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ከማሳደግ ባሻገር የንግዱን ስርዓት ቀልጣፋ ውጤታማ ያደርገዋል ብለዋል።












## ባለስልጣኑ 29 አገልግሎቶችን በመሶብ ማዕከል አካቶ እየሰራ ይገኛል፡- አቶ አደም ገቢ (በባለስልጣኑ የመሶብ ማዕከል አስተባባሪ)



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን 29 የሚሆኑ አገልግሎቶችን በመሶብ ማዕከል አካቶ እየሰራ ይገኛል ሲሉ በባለስልጣኑ የመሶብ ማዕከል አስተባባሪ የሆኑት አቶ አደም ገቢ ገለፁ።

በመሶብ ማዕከል ውስጥ 23 የሚሆኑ የፌደራል ተቋማት ተካተው እየሰሩ መሆኑን ገልፀው እነዚህ ተቋማት እርስ በእርስ ትስስር ፈጥረው ሁሉንም አገልግሎት በአንድ ማዕከል ውስጥ በማካተት ለተገልጋዩ በተሳለጠና ዲጅታላይዝ በሆነ መንገድ አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ ብለዋል።

የመሶብ አገልግሎት የተገልጋዮችን እንግልት ከመቀነስና ካላስፈላጊ ወጪ እንዲሁም ከጊዜ አንፃር የሚደርስባቸውን ችግር ለመቅረፍ ትልቅ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

አቶ አደም አያይዘው መሶብ አገልግሎት ከሌላው ዲጅታላይዜሽን ሲስተም የሚለየው በፌደራል ተቋም

PAGE 3

## ከገፅ 2 የዞረ

የሚሰጡ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ተቋም በማስተሳሰርና በማካተት አገልግሎቱን ማሳለጥ መቻሉ ነው ብለዋል፡፡

በመሶብ አገልግሎት ለወደፊት ተገልጋዩ በማዕከሉ መምጣት ሳይጠበቅበት ባለበት ሁኖ አገልግሎቱን እንዲያገኝ የሚደረግበት ሲስተም እየተዘረጋ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

እንደ ሀገር በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ከዲጅታላይዜሽን ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ ይዞ የሚመጣው የመልካም አስተዳደር ችግር አለ እነዚህን ችግሮች ሊቀርፍና ሙሉ በሙሉ ሊያስቆም የሚችለው ሁሉንም አገልግሎታችንን ዲጅታላይዝ አድርገን ተገልጋዩ ከእኛ ጋር መምጣት ሳይሆን እኛ ተገልጋዩ ጋር መድረስ ስንችል ነው ያሉት አቶ አደም ገቢ የመሶብ አገልግሎት ዋና ዓላማም ማሳያውም ጅማሮውም ይህ ነው ብለዋል፡፡ በተለይም ተገልጋዩ ከዚህ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ከቴክኖሎጂ ጋር ያለው ቀረቤታ እንዲያድግ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል፡፡




## ለብሔራዊ ጥቅማችን መረጋገጥ የሰራተኛው ሚና የጎላ ነው ፡- ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በብሔራዊ ጥቅም እና የጂኦስትራቴጂ ቁመና በሚል ሀገራዊ አጀንዳ ላይ የተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች በተገኙበት ውይይት አካሂዷል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በመክፈቻ ንግግራቸው ፤ ሃገራችን ኢትዮጵያ ትልቅ የህዝብ ቁጥር፣ ትልቅ የቆዳ ስፋት፣ በርካታ የተፈጥሮ ሀብት፣ ወሳኝ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ያለት ቢሆንም በጂኦስትራቴጂው ምህዳር ውስጥ ብሔራዊ ጥቅሟ ሳይከበርላት የቆየች ሀገር ናት ብለዋል፡፡

የብሔራዊ ጥቅምና ጂኦስትራቴጂያዊ ቁመና አጀንዳችን የሀገር፣ የህዝብና የትውልድ አጀንዳ መሆኑን በመረዳት ሁሉም ሰራተኛ ሚናውን መጫወት አለበት ብለዋል ፡፡

የተቋማችንን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በትንንሽ ችግሮች ሳንበገር ስራዎቻችንን በታታሪነትና በውጤታማነት ለመፈፀም በትኩረት መስራት አለብን በማለት አስገንዝበዋል ፡፡

ወደ ገፅ 4 ዞሯል

ከገፅ 3 የዞረ

የባለስልጣኑ የዕፅዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወንዳለ ሀብታሙ (ዶ/ር) በህዳሴ ግድብ ግንባታ ፣ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ የተጀመረው ግዙፍ የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ እና በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጥሮ ጋዝ መጠቀም የቻልንበትን አቅምና እና ስኬት በማስቀጠል ሀገር ያለ ብሔራዊ ጥቅም እንደማትቀጥል በመገንዘብ ሁላችንም ለብሔራዊ ጥቅም እና የጂኦስትራቴጂ ቁመና መረጋገጥ በጋራ መቆም አለብን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አክለውም ጠንካራ የሬጉላቶሪ ተቋም ለመገንባት የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የሰው ሀብት አቅም የመገንባት ተቋሙ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡







## ባለስልጣኑ የእፅዋት ጤና አጠባበቅ ማስተግበሪያ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ይፋ አደረገ፡፡









ወደ ውጪ የሚላኩ የዕፅዋት ምርቶች ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የጠበቁ እንዲሆኑና ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ የሚያስችል የ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ መዘጋጀቱን የግብርና ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ሀላፊዎች፣ ከአለም የምግብና እርሻ ድርጅት ኃላፊዎች፣የክልል ግብርና ቢሮ ሀላፊዎች፣ የክልል የዕፅዋት ጥበቃ ላቦራቶሪ ሀላፊዎችና ከፌደራል የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት አውደ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደተናገሩት፤ የግብርና ምርቶች ወደ ዓለም ገበያ ሲላኩ ከበሽታ ነጻ መሆናቸውንና ጥራታቸውን የማረጋገጥ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከዓለም አቀፍ የንግድ መመዘኛ መስፈርቶች አንጻር ምርቶች

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

ከእርሻ ጀምሮ ወደ ውጭ እስከሚላኩበት ባለው ሂደት ውስጥ ያሉ ክፍተቶች ላይ ጥናት መደረጉን ተናግረዋል።

በጥናቱም በዘርፉ የሰለጠነ የባለሙያ እጥረት፣ የላብራቶሪ አለመሟላት፣ የሀብት እጥረትና ረጅም ዓመት የቆየና ከጊዜው ጋር ያልዘመነ የህግ ማዕቀፍና የቴክኖሎጂ ክፍተቶች መለየታቸውን ገልፀዋል ።

እነዚህን ክፍተቶች ማሟላት የሚያስችል የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ መዘጋጀቱን ጠቅሰው፤ በአጭር ጊዜ ወደ ተግበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የባለስልጣኑ የዕፅዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወንዳለ ሀብታሙ(ዶ/ር)፤ ስትራቴጂ ዕቅዱ ወደ ውጭ የሚላኩና ወደ ሀገር የሚገቡ የዕፅዋት ምርቶች በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነታቸውን የሚያሳድግና ተወዳዳሪ እንድሆኑ የሚያስችል ነው ብለዋል።

በአለም የምግብና እርሻ ድርጅትየኢትዮጵያ ፅ/ቤት ሃላፊ እና የምስራቅ አፍሪካ ተወካይ የሆኑት ፋራይ ዚሙድዚ በበኩላቸው፤ በጋራ የተዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂ እቅዱ በውጤታማነት እንዲተገበር ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የዕፅዋት ደህንነት ጥበቃ በተገቢው እንዲጠናከርና ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ በዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ ተሳታፊ እንዲትሆን ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

ባለስልጣኑ በ2017 ብጀት ዓመት በእንስሳት ምርት ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል በ13 የጥራት ምርመራ አይነቶች ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘ ሲሆን በቅርቡ በዕፅዋት ዘር ፍተሻ ላቦራቶሪ ዓለም አቀፍ እውቅና ለማግኘት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው።

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አመታዊ የደም ልገሳ መርሃ ግብር አካሄደ።






የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በየዓመቱ የሚያካሂደውን የደም ልገሳ መርሃ ግብር **"ደም እንለግስ ፤ ተስፋን እንስጥ! "** በሚል መሪ ቃል አካሂዷል።

ባለስልጣኑ ሰራተኛውን በማስተባበር ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን በቋሚነት በመርዳት ፣ ለት/ቤቶች አጋዥ መፃህፍትን በመለገስ ፣ በየአመቱ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በማካሄድ እንዲሁም የደም ልገሳ ፕሮግራም በማካሄድ የሰብዓዊነት እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራዎችን ትኩረት ሰጥቶ እያከናወነ ይገኛል ።

የደም ልገሳ መርሃ ግብሩን ያስተባበሩት የባለሥልጣኑ የሴቶች ጉዳይ ማህበራዊ አካቶ ትግበራ ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ትዕግስት ወልደአገኘሁ ሲሆኑ፤

ከ ገፅ 5 የዞረ



አንድም ሰው በደም እጦት ምክንያት መሞት የለበትም በማለት በየአመቱ በመደበኛነት ደም በመለገስ የሰብዓዊና በጎ ተግባር እየተከናወነ መሆኑን ገልፀዋል።

ወ/ሮ ትዕግስት አክለውም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ልገሳን ባህል በማድረግ ሁሉም የተቋሙ ሰራተኛ ደም የሚያስፈልገውን የወገኑን ህይወት እንድታደግ ሰብአዊ ጥሪ አቅርበዋል ።

በዕለቱ ደም በመለገስ የተሳተፉት የተቋሙ ስራተኞች በበኩላቸው በደም እጥረት ምክንያት የሚገጥሙ የሰው ልጆች ስቃይና ህልፈትን ለመታደግ በየአመቱ በሚካሄደው የደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ ደም በመለገስ የድርሻችንን እንወጣለን ብለዋል።

በደም ልገሳ ፕሮግራሙ ላይ የተቋሙ የሥራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ተሳትፈዋል ።

## የመመሪያዎች መዘጋጀት የቁጥጥር ስራዎችን በማጠናከር ደህንነቱ፣ ጥራቱና ፈዋሽነቱ የተጠበቀ የእንስሳት መድሀኒት ለተጠቃሚው እንዲደርስ ወሳኝ ሚና አለው:- አምባሳደር ድሪባ ኩማ (ዋና ዳይሬክተር)



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከ SNV, FSRP, IFC WBG, UK VMD ጋር በመሆን ለእንስሳት መድሀኒት ሪጉላቶሪ የሚያስፈልጉ የአሰራር መመሪያዎች እና ቴክኒካል ጋይድላይኖች በስፋት እየተዘጋጁ ፀድቀው በስራ ላይ እየዋሉ መሆኑንና ቀሪዎቹን ግብዓት እያሰባሰቡ መሆኑን ገለፀ።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በመክፈቻ ንግግራቸው እነዚህ መመሪያዎችና ጋይድላይኖች ሲዘጋጁ በፊት ከነበረው የአሰራር ስርዓት በተሻለ የቁጥጥር ስራው ግልፅነት ያለውና የተጠናከረ እንዲሆን ያግዛል ብለዋል። በተለይም በእንስሳት መድሀኒት ንግድ በተሰማሩ

ድርጅቶች ላይ የቁጥጥር ስራዎችን በማጠናከር ደህንነቱ፣ ጥራቱና ፈዋሽነቱ የተጠበቀ የእንስሳት መድሀኒት ለተጠቃው ተደራሽ እንዲሆን ወሳኝ ሚና አለው ብለዋል።

በባለስልጣኑ የእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ሰለሞን ከበደ በበኩላቸው የአሰራር መመሪያዎች እና ቴክኒካል ጋይድላይኖች በስፋት የተዘጋጁ ሲሆን በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1022/2016 በባለስልጣኑ ተዘጋጅቶ በፍትህ ሚኒስቴር ቁጥር ተሰጥቶት የጸደቀ መሆኑን ገልፀዋል።

በተጨማሪም የእንስሳት መድሃኒት ምዝገባ መመሪያ 1036/2017 በባለስልጣኑ ተዘጋጅቶ በፍትህ ሚኒስቴር ቁጥር ተሰጥቶት መፅደቁን ተናግረዋል።

ዶ/ር ሰለሞን አክለውም ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ቴክኒካል የአሰራር ጋይድላይኖች ስለሚያስፈልጉ 5 ጋይድላይኖች ማለተም አዲስ የእንስሳት መድኃኒት ምዝገባ ጋይድላይን፣ አዲስ የእንስሳት ክትባት ምዝገባ ጋይድላይን፣ የእንስሳት መድኃኒት ምዝገባ ጋይድላይን እና የእንስሳት መድኃኒት ለውጥ ምዝገባ ጋይድላይን እንዲሁም የእንስሳት ህክምና መሳሪያ ምዝገባ ጋይድላይን ተዘጋጅተው መፅደቃቸውን ገልፀዋል።

በተጨማሪም አንድ የገበያ እጥረት ያለባቸው የእንስሳት መድሃኒቶች ምዝገባ ጋይድላይን (Minor use veterinary drugs registration guideline) እና ሁለት መመሪያዎች ማለትም የእንስሳት መድሃኒት ቁጥጥር እና አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ረቂቅ መመሪያ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሣሪያዎች አስመጪ፤ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ለአሰራር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ተሰብስበዋል።

PAGE 7

**በእንስሳት መኖ ላይ የሚታየውን የጥራትና ደህንነት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት ወሳኝ መሆኑ ተገለጸ።**

በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የእንስሳት ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ከSNV ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የለዘርፉ ባለሙያዎች በእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ማስጠበቅ ላይ ያተኮረ ስልጠና ለተከታታይ ሶስት ቀናት እየሰጠ ይገኛል።

በግብርናው ዘርፍ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባሻገር ጥራትና ደህንነቱ የተጠበቀ የእንስሳት መኖ ለእንስሳት ምርቶች ደህንነትና ለማህበረሰቡ ጤና መጠበቅ ሚናው የጎላ በመሆኑ በዘርፉ የጥራትና ቁጥጥር ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው ።

በስልጠናው ላይ የተገኙት በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የእንስሳት ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ዘላለም አበበ፤የስልጠናው ዋና አላማ የመኖ ጥራትና ደህንነት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ የመኖ ጥራትና ደህንነት የቁጥጥር ስራ ላይ የሚሰሩ የባለሙዎችን አቅም ለመገንባት ነው ብዋል።

በመልካም የመኖ አመራረት ልምድ (GMP) እና የመልካም የንጽህና ተግባራት (GHP) ላይ አንድ መኖ አቀነባባሪ ድርጅት የመኖ ጥሬ እቃውን ከቅበላ ጀምሮ አቀናብሮ ጥራትና ደህንነቱን ተጠብቆ ለተጠቃሚ እስከሚያቀርብበት ድረስ ያለውን እሴት ሰንሰለት ተጠብቆ የመኖውን ጥራትና ደህንነት እንዴት እየጠበቀ ነው የሚለውን ከSNV ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በተዘጋጀው የአጋርነት ሰነድ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ስልጠናው በአፅንኦት ለዘርፉ ባለሙያዎች እየተሰጠ መሆኑን አብራርተዋል።

በእንስሳት መኖ ላይ የሚስተዋለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የመጀመሪያ ዙር ስልጠና በዋናው መ/ቤት ለሚገኙ የመኖ ሬጉላቶሪ ባለሙያዎችና ለእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች እየተሰጠ መሆኑንና በሁለተኛው ዙር በማዕከላትና በኳራንታይን በጣቢዎች ላሉ የመኖ ኢንስፔክተሮችና ለመኖ አቀነባባሪዎች እንደሚሰጥ አቶ ዘላለም ገልጸዋል።ስልጠናውን የሰጡት በSNV ኢትዮጵያ አመቻችነት ከኔዘርላንድ ከብለስ ዴሪ ኢንተርናሽናል ካምፓኒ ኮርኔልስ ሶኔቮልድ ሲሆኑ፤ *የዛሬው መኖ የነገው የሰው ልጅ ምግብ * በመሆኑ ለመኖ ጥራትና ደህንነት መረጋገጥ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በባለስልጣኑ ወደ ሀገር በሚገቡና በሚወጡ የግብርና ምርቶችንና ግብዓቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እያደረገ መሆኑ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእፀዋትና ከእፀዋት



ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች እና የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የጥራት እና ደህንነት ላይ ቁጥጥር ስራ እየሰራ ይገኛል።

ባለስልጣኑ አሰራሩን በማዘመንና ለተገልጋዮች ምቹ በማድረግ ሁሉንም አገልግሎቶች ዲጂታላይዘድ ያደረገ ሲሆን በጣቢያዎችም አብዛኞቹ አገልግሎቶች በዲጂታል ስረዓቱ እየተሰራበት ይገኛል።

ባለስልጡኑ ወደ ሀገር በሚገቡና በሚወጡ የግብርና ምርቶችና ግብዓቶች ላይ ቁጥጥር ከሚያደርግባቸው ጣቢያዎች መካከል በሞጆ ደረቅ ወደብ ውስጥ የሚገኘው የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ሞጆ ጣቢያ አንዱ ነው። በባለስልጣኑ የሞጆ ጣቢያ ሀላፊ የሆኑት ዶ/ር ዳንኤል ጌታቸው፤ በጣቢያው የእንስሳት መድሀኒት፣ የእንስሳት መኖ ፣ ጸረ- ተባይና ማዳበሪያ ፣ ስጋና የስጋ ተረፈ ምርቶች ላይ መስፈርቱን ያሟሉና ጥራትና ደህንነታቸው የተረጋገጠ መሆንን በማረጋገጥ የተጠናከረ የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ስራ እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በዕፅዋትና የዕጽዋት ዉጤቶች ላይ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡት ላይ ብቻ ቁጥጥር እንደሚያደርጉም ተናግረዋል።

የቁጥጥር ስረዓቱ በኦንላይን ሲስተም የሰነድ ፍተሻ ከተደረገ በኃላ ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን ለባለስልጣኑ የእንስሳት ምርት ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ሳምፕል በመውሰድ ጥራቱንና ደህንነቱ የማረጋገጥ ስራ እንደሚሰራ አስረድተዋል።

ቁጥጥር በሚደረግበት ወቅት የጥራትና የደህንነት ችግሮች ሲያጋጥሙ በመውጫና መግቢያ መመሪያዎች መሰረት ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ከባለስልጣኑ ጋር በመነጋገር አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስዱ ገልፀዋል።

እስካሁን ድረስ በነበረው የቁጥጥር ሂደት ሶስት የእንስሳት መድኃኒት አስመጭ ድርጅቶች በመግቢያና መውጫ መመሪያ 02/2009 የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው ባለመገኘታቸው መድኃኒቶቹ በሀገር ዉስጥ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ገልጸዋል።

በመጨረሻም ዶ/ር ዳንኤል የቁጥጥር ስርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰሩ መሆኑን አንስተዋል።

# ቡፌ ሽሦሡጁ

## አዝናኝና አስተማሪ ቀልዶች

ብዙ ሰካራሞችን የጫነ አውሮፕላን በረራ ላይ ነው፤

ሰካራሞቹ በጣም ይጮሃሉ፡ ይረብሻሉ፥

በዚህመሃል

አንድ ሰካራሙም ፓይለቱ ጋራ ይሄድና ማብረር

አስተምረኝ እያለ

ይጨቀጭቀዋል

ፓይለቱም ፤ ችግር የለውም የሚረብሹትን ዝም

ካስባልካቸው አለማምድካለው ይለዋል

ሰካራሙም ወደ

ሰካራሞቹ ይሄድና ዝም አስብሎአቸው ይመለሳል::

ፓይለቱም በጣም በመገረም ምን ብለሃቸው ነው

እንደዚህ ጭጭ ያሉት ብሎ ይጠይቃል...

ሰካራሙም፡ የአውሮፕላኑን በር ከፈትኩና፡ ውጭ

ወጥታቹ ተጫወቱ ብያቸው







## የታላላቅ ሰዎች አባባል

1.ከሰዎች ጋር ሮጠህ ያልደረስክበት ነገር ካለ ወደ ተነሳህበት ተመልሰህ

ከፈጣሪህ ጋር መሮጥ ጀምር፣ ያኔ ካሰብክበት ሳይሆን ካሰበልህ ቦታ ትደርሳለህ።

2. በአብዛኛው ጊዜ ሴቶች የፍቅርን ትርጉም የሚጠፋባቸው በውበታቸው

ማምለክ ሲጀምሩ ሲሆን ወንዶች ደግሞ በገንዘባቸው ማምለክ ሲጀምሩ

ነው።

3. መጀመሪያ ለራስህ ራስህ መሆን ስትጀምር ለማን ምን መሆን

እንዳለብህ ትገነዘባለህ።

4. የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታው ሲጨምር የጓደኞቹን ብዛት ይቀንሳል።

5. ዝቅተኛ እውቀት ባለህ ቁጥር የምትተኛው እንቅልፍ ከፍተኛ ይሆናል።




